Seattle
**Youth Violence Prevention**
Initiative

# በሲያትል የወጣቶች ብጥብጥ ማስወገጃ ዛሳብ እንቅስቃሴ

## መንደርደሪያ ዛሳብ

የሲያትል ወጣቶች ብጥብጥ ማስወገጃ ዛሳብ እንቅስቃሴ (ኢንሽየቲቭ) የወጣቶች ብጥብጥ ጉዳይን ከቤት አፈራሽ ፤ ከወጣትና ከማህበረተሰብ ከተዘጋጁ ፕሮግራሞች ጋር በማቀናጀት በማስረጃ የተመሰረቱ ስልቶችን በሚያካልል አጠቃላይ አቀራረብ እየታገለ ነው። በሲያትል ውስጥ በዓመታት ከታዩት በአጠቃላይ የቀነሱ የወንጀል ቁጥሮች ቢታዩም ፤ የወጣት ኃይለኞነት ወንጀል ድርጊቶች ቁጥር አሳሳቢ የማህበረተሰቡ ጉዳዮች መሆናቸው እንደቀጠለ ነው። ከተማው ለወጣት ብጥብጥና መፍትሔ የሚያገኝበትን መንገድ ባንዴ ለመለወጥ በሐምሌ 2009 ውስጥ የዛሳብ እንቅስቃሴውን ጀምሯል።

## ግቦች

የዛሳብ እንቅስቃሴ ግቦች በብጥብጥ የተነሳ ወጣቶች ፍርድ ቤት መቅረባቸውን በ50 በመቶ ለመቀነስና ከብጥብጥ ጋር በሚገናኙ ድርጊቶች የተነሳ ወጣቶች ከመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መታገዳቸውንና መባረራቸውን በ50 በመቶ ለመቀነስ ነው።

## ብቁ የሚሆኑት ማናቸው?

እንቅስቃሴው የሚያተኩረው በ1500 ወጣቶ ች እድሜያቸው ከ12 እስከ 17 ሆኗቸው ፤

- በኃይለኛነት ብጥብጥ በመፈጸማቸው የተፈረደባቸውና ከእስር የተፈቱ ፤
- ተይዘው ግን ታስረው ያልቆዩ ፤
- የመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሆነው ከፋኛ ማጋጣ ሊሆኑ የሚችሉ ወይም በብርቱ የበጥባጭ ባህርይ ምክንያት በብዛት ከትምህርት ቤት እንዲታገዱ የሆኑ ፤ እና/ወይም
- በመኖሪያ ሠፈራቸው የብጥብጥ ተጠቂዎች የነበሩ።

አገልግሎቶቹ የሚያስፈልጊቸው ወጣቶች መጠን ሰፊ ሲሆን፥ የሚያስፈልጊቸውም አገልግሎቶች ይለያያሉ። በጣም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ወጣቶች ከፍተኛ በሕክምና የተመረኮዙ አገልግሎቶች ያገኛሉ። ሌሎች በጎ ምርጫዎችን ማድረግ የሚያስችሏቸውን ዕድሎች እንዲያገኙ የሚረዷቸውን አገልግሎቶች ያገኛሉ።

የሲያትል የዛሳብ እንቅስቃሴ የሌሎች ከተማዎችን ስኬታማ የብጥብጥ ማስወገጃ ፕሮግራሞችን መመሪያዎችንና አንዳንድ ነጥቦችን ያካትታል። ከሌሎች ከተማዎች የጎላውና ግልጹ የማያወላውለው መልዕከተ መንግሥት ሁሉንም የዛሳብ እንቅስቃሴ ዕቅድ ዝርዝሮችን መጻፍ አያስፈልገውም የሚል ነበር። ይህን ምክር በመጠበቅ ከተማው በማህበረተሰብ አመራር የተገነባ ዕቅድ አውጥቷል። ይህም የተፈጸመው በማህበረተሰብ የተመረኮዘ በማዕከላዊ ፤ በደቡብ ምሥራቅ ፤ እና በደቡብ ምዕራብ ሲያትል ውስጥ የተቋቋሙ ሦስት የመኖሪያ ሠፈር መዋቅሮችን የሚመሩ ወኪሎችን በባልደረባነት በማቋቋም ነው።

## የመኖሪያ ሠፈር መዋቅር ወኪሎች ማናቸው?

የእንቅስቃሴ ጥረቱን የሚያስተባብሩት መሪ ወኪሎቹ ፤ ቴራፒቲክ ሔልዝ ሰርቪስስ ፤ ሳውዝዌስት ዩዝ ኤንድ ፋሚሊ ሰርቪስስ ፤ እና በሬይነር ቪስታ ቦይስ ኤንድ ገርልስ ክለብ የሚመራ
ወኪል ድርጅቶች ማህበር ናቸው።

## አገልግሎቶቹ ምንድን ናቸው?

ወጣቶች በትምህርት ቤቶች ፤ በማህበረተሰብ ወኪል ድርጅቶች ፤ በወጣት ፍርድ ቤት ፤ በፖሊስ ፤ በጎዳና እርዳታ ሰጪ ሠራተኞች ፤ እና በሲያትል ፓርክስ ኤንድ ሪክርኤሽን ዩዝ ሴንተርስ በኩል ለአገልግሎቶቹ ይላካሉ። በማህበረተሰብ ደረጃ የሚጠናቀሩት የአገልግሎት ስፋቶች የሚያጠቃልሉት ፤

- በጎዳና እርዳታ ማቅረብ (ስትሪት አውትሪች)
- ጉዳይን ማስተናገድ (ኬዝ ማኔጅመንት)
- ጠብ ጫሪነትን የመተካት ስልጠና
- ክትትል (ሞኒተሪንግ)
- ለወጣቶች ሥራና ስልጠና
- ብቁ የሚሆኑ ወጣቶችን የሚያገለግሉ የ"ኔበርሑድ ማቸንግ ፈንድ" ፕሮጀክት
- በወጣቶች ለተዘጋጁ ፕሮግራሞች የተራዘሙ "የፓርክ ዩዝ ሴንተርስ" ሰዓቶች

በተጨማሪም የ"ሶፍት ዩኒፎርም" በትምህርት ቤት ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ሹሞች ለአራት መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፤ ለአኪ ኩሮስ ፤ ለዴኒ ፤ ለመርሰር ፤ እና ለዋሽንግተን ሚድል ስኩል ተመድበዋል። የዛሳብ እንቅስቃሴው ሌላው ወሳኝ ክፍል ወጣቶችን "ባሉበት ቦታ" የሚያገኝ ስለ ጎዳና ሁኔታ ታማኝነትን ያተረፈ ግለሰቦችን የሚያቅፍ የጎዳና እርዳታ ሰጪ ቡድን ነው። ትምህርት ቤት-ነክ ሹሞችና የጎዳና እርዳታ ሰጪ ሠራተኞች ዛሳቦችን ያዳምጣሉ ፤ ለወጣቶች መመሪያ ፤ መረጃ ይሰጣሉ ፤ ውዝግብን በመፍታት ወጣቶችን ይረዳሉ ፤ እንዲሁም ጤናማ ፤ በጎ ምርጫዎችን ወጣቶች እንዲወስዱ ያበረታታሉ።

የዛሰብ እንቅስቃሴው ከመጀመሩ በፊት ፤ የሲያትል ፖሊሶች የማጠንከሪያ ቁጥጥራቸውን ከፍ አድርገው ነበር ፤ ይህም በ"ጋንግ ዩኒት" ውስጥ የሚሠሩትን የፖሊሶች ቁጥር እጥፍ አድርጎታል። አዲስ የቀን ተነጣይ ጓድ (ጋንግ ስኳድ) የማታዎቹን ሁለት ተነጣይ ጓዶች ለማገዝ በትምህርት ቤቶች አካባቢ የጥበቃ ሥራ ያካሂዳል።

## ሥራ ማስኬጃ ገንዘብ

ከተማው በ2009 እና በ2010 ወቀት ለእንቅስቃሴው 8 ሚሊዮን ዶላር በሥራ ላይ እያዋለ ነው ፤ ይህም በዚህ በራሪ ጽሑፍ ላይ ለተዘረዘሩት አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች ይከፍላል።

## ለተጨማሪ መረጃ

**ማሪኮ ሎክሃርት**
ዲሬክተር ፤ የሲያትል ዩዝ
ቫዮለንስ ፕረቨንሽን ኢኒሽየቲቭ
mariko.lockhart@seattle.gov
206-233-7915

**ጃሚላ ቴይለር**
ሴንተራል ኔበርሑድ
ኔትዎርክ ኮኦርዲኔተር
michaelg@THS-WA.org
(206) 323-9014

**ሮበርት ግራንት** ሳውዝዌስት
ኔበርሑድ ኔትዎርክ ኮኦርዲኔተር
nfatuesi@swyfs.org
206-937-7680 ext. 109

**ሔዲ ሔንድርሰን-ልውስ**
ሳውዝኢስት ኔበርሑድ
ኔትዎርክ ኮኦርዲኔተር
mpatu@positiveplace.org
206-436-1898

**በዌብ ላይ ፤**
www.safeyouthseattle.org